# በአዲስ አበባ ከተማ ላይ በዘረኞች የታወጀው ጦርነት በአስቸኳይ ይቁም!!

## ከመላው ኢትይዮጵያ

### የባህል፤ የትምህርትና የዕርዳታ ድርጅት

**<u>መጋቢት 4 ቀን 2011 ዓም</u>**

ላለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት በሕወሓትና ሻዕቢያ ተውጥኖ በዘር አደራጅተው ያሰለጥኗቸው የጎሣ ፖለቲካ ድርጅቶች እንዲያስፈጽሙት የተሰጣቸው ኢትዮጵያን የማፍረስ ተግባር መደምደሚያ ነው በማለት አዲስ አበባ ላይ ያወጁትን ግልጽ ጦርነት እኛ በካናዳ ብሪቲሽ ኮሎምብያ ቫንኮቨር የምንገኝ የኢትዮጵያ የባህል፤ የትምህርትና የዕርዳታ ድርጅት አጥብቀን እናወግዛለን።

አዲስ አበባ ከመልክዐ ምድራዊ አቀማመጧ ጀምሮ ተፈጥሮ የኢትዮጵያ ማዕከል ነች። ከአራቱም አቅጣጫ የኢትዮጵያ ጠረፍ ወደ አዲስ አበባ ቢለካ የርቀታቸው ተመሳሳይነት ማዕከላዊነቷን ይመሰክራል። እንደ ማዕከልነቷ ሁሉ ለሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች መዳረሻ በመሆኗ በታሪካዊ ዕድገቷ የሁሉም አሻራ ያረፈባት ነች።

አዲስ አበባችን የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳትሆን የመላው ጥቁር ሕዝብ በቅኝ ግዛት በሚማቅቅበት ወቅት የነፃነት ተምሳሊት በመሆን ከሰሕጢና ዶጋሊ ቀጥላ የአውሮጳ ቅኝ ገዥዎችን ክንፍ ለመሰባበር የተመከረበትና ጦር ያዘመተች፤ ለነፃነታቸው የሚታገሉ አፍሪቃውያን ያስተማረች፤ ያሰለጥነች አለኝታ በመሆን የቅኝ ገዥዎችን ተፅዕኖ በመቋቋም የአፍሪቃ አንድነት ድርጅትን ማቆም ብቻ ሳይሆን አፍሪቃዊነትን በእያንዳንዱ የዓለማችን ጥቁር ሕዝብ ልብ ውስጥ የአንድነት ማኅተም ያተመች ከተማ ነች።

ይህንን መላው ኢትዮጵያዊ በጋራ የመሠረታትን፤ የዘር፤ የኀይማኖት፤ የቋንቋ ልዩነት የማትታውቅ ዓለም አቀፍ ከተማ በአንድ ጎሣ የበላይነት እንድትተዳደር የታለመውን የቁም ቅዠት ስንሰማ በአገራችን የሰፈነው ዘረኝነትና እጅግ የወውረደ ኋላ ቀር አስተሳሰብ መኖሩ  አሳዝኖናል።

ለዚህ አስተሳሰብ መነሻው እኔ “ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል” የሚለው ሕወሓት በ1997ዓም የአዲስ አበባ ሕዝብ በአንድ ድምጽ ወያኔን አልፈልግም ብሎ በምርጫ አሽቀንጥሮ ስለተፋው በኦሕዴድ በኩል የብቀላ አስተሳሰብ ሰጠው። አሁንም የወያኔ አገዛዝ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነፃነቱና ለዲሞክራሲ ለውጥ ቆርጦ በመነሳቱን የተገነዘበው ዘረኛው አገዛዝ አዲስ አበባን እራሱ በፈጠረው ድርጅት ኦሕዴድና ኦነግን በመሣሪያነት ተጠቅሞ በታላቁ የኦሮሞ ብሔረሰብ ስም በአዲስ አበባ ከተማና በኢትዮጵያ አንድነት ላይ አደጋ ደቅኗል። የዘረኝነትና የዘር ማጽዳት ወንጀል ልምምዱን በለገጣፎ የጀመሩ በመሆናቸው ከአገር ቤት የሚመጡ ዘገባዎች እየጠቆሙን ነው። እኛም ሁኔታው እጅግ ስላሳሰበን የሚከተሉትን ጥያቄዎች እያቀረብን ከአገር ውጪ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንዲረባረቡ በታላቅ አክብሮት እንጠይቃለን።

1. አዲስ አበባ ከተማ ዓለም አቀፍ፤ አፍሪቃ አቀፍና የመላው ኢትዮጵያውያን ከተመ እንደመሆኗ ሁሉ የከተማው ከንቲባ ይህንኑ ሊያሟላ የሚችል በነዋሪዎቿ እንዲመረጥ።
2. የአዲስ አበባ አስተዳደር ክልል ወያኔ አዲስ አበባን ከመቆጣጠሩ በፊት በነበረው መናገሻ አውራጃ እንዲሆን።
3. አቶ ለማ መገርሳና ዶክተር ዓቢይ አሕመድ ይህንን በሚመለከት በቂ ማብራሪያ እንዲሰጡና ከዘረኝነት አስተሳሰብ አዲስ አበባን ነፃ መሆኗን እንዲያረጋግጡ።
4. በባዕዳን ተቀጥረው ኢትዮጵያን ለማፈራረስ የቆሙ ኃይላት ለኦሮሞ ተቆርቋሪ በማምሰል የኦሮሞን ስም እያጥፉ በመሆኑ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እንዲያወግዘው እንጠይቃለን።

የመላው ኢትዮጵያ የባህል፤ የትምህርትና ባህል ማኅበር
ካናዳ ብሪቲሽ ኮሎምቢያ
ቫንኩቨር